3.3.1/362/10
02 ታህሳስ 2010

**ለጉምሩክ ሥነስርአት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች**
**<u>በያሉበት</u>**

የንግድ ሚኒሴቴር ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ/ም በቁጥር 01.1.35/1203 በተፃፈ ደብዳቤ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርት የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 013/2010 ከህዳር 18 ቀን 2010 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የገለጸበትን 1 ገጽ ደብዳቤና 6 ገጽ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርት የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ በድምሩ 7 ገጽ ለተገቢው አፈፃጸም የላክን መሁኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሰብለ ገብሩ
የጉምሩክ ጉ/ቅ/ጽ/ቤቶች
ድጋፍና ክትትል ቡድን አስተባባሪ

**<u>ግልባጭ፤</u>**

- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት (አባሪ 7 ገጽ)

**<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
**Ministry of Trade**

ዝቅ 1A00
28-03-10

ቀን 26 ህዳር 2010
Date

ቁጥር 01/1/35/1203
Ref. No.

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 013/2010 ስለመላክ፡፡</u>

ላኪዎች ለውጭ ገበያ ከሚያዘጋጁቸው የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች በኩንታል የሚወጣውን የብጣሪ መጠን በጥናት በመለየት እና በመመሪያ በመደንገግ ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲውል ለማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤታችን የተዘጋጀው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 013/2010 ከህዳር 18 ቀን 2010 ዓ/ም ጀምሮ የፀደቀ በመሆኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የመመሪያውን 1ቅጅ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

"ከሰላምታ ጋር"

እያሱ ዘውዴ
ሚኒስትር ዴኤታ

☎ +251-11-551 80 25-29
✉ 704
Fax +251-11-551 54 11
+251-11-553 1027
+251-11-552 2419
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር

## ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 13/2010

ህዳር 2010 ዓ/ም

አዲስ አበባ

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

# ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 13/2010

በየምርት ዘመኑ በላኪዎች በተገዛው፣ በብጣሪ መልክ በወጣው፣ ወደ ውጪ በተላከው እና በቀረው የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች መጠን መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት የምርት ቆጠራ ሚዛን ለመስራት፣ የገቢ ግብር ለማስላት እና ጥቅም ሊሰጥ የሚችለውንና የማይችለውን ብጣሪ በመለየት ውሳኔ ለመስጠት እንዲውል በማስፈለጉ፣

አዳዲስ ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች በመኖራቸው፣

ይሰራበት የነበረው የብጣሪ መጠን አነስተኛ በመሆኑና ማስተካከል በማስፈለጉ፣

ይህ መመሪያ በሰሊጥና ነጭ ቦለቄ የግብይት ደንብ ቁጥር 178/2002 አንቀጽ 27 እና በጥራጥሬ ምርቶች የግብይት ደንብ ቁጥር 377/2008 አንቀፅ 22 ላይ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ወጥቷል።

## አጠቃላይ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች የብጣሪ መጠን አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 13/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

2.1. "ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች" ማለት በማበጠሪያ ማሽን ወይም በእጅ ተለቅመው በጥራት ከተዘጋጁ በኋላ ወደ ውጪ የሚላኩትን ሰሊጥ፣ ኑግ፣ የጉሎ ፍሬ፣ ለውዝ፣ የዱባፍሬ፣ ተልባ፣ ጎመንዘር፣ ሱፍ እና ወደፊት ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች ተብለው የሚወሰኑትን ይጨምራል፤

2.2. "ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የጥራጥሬ ምርቶች" ማለት በማበጠሪያ ማሽን ወይም በእጅ ተለቅመው በጥራት ከተዘጋጁ በኋላ ወደ ውጪ የሚላኩትን ቀይ ቦሎቄ፣ ነጭ ቦሎቄ፣ ቀይና ነጭ ዥንጉርጉር ቦሎቄ፣ ሌሎች ቦሎቄዎች፣ ፒገን ቢን፣ ፒንቶ ቢን፣ ሽምብራ፣ አኩሪ አተር፣ ግብጦ፣ ማሾ፣ ባቄላ፣ ጓያ፣ ምስር እና

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives

ወደፊት ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የጥራጥሬ ምርቶች ተብለው የሚወሰኑትን ሁሉ ይጨምራል፤

2.3. "ብጣሪ" ማለት ለውጪ ገበያ ከሚዘጋጁ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች ውስጥ በምርት ዝግጅት ወቅት የሚወጣ ስብርባሪ ፍሬ፣ ቀለሙን የቀየረ/የገረጣ ፍሬ፣ የተጨማደደ ፍሬ፣ የቀጨጨ ፍሬ፣ የነቀዘ ፍሬ፣ የሻገተ ፍሬ፣ ገለባ ወይም ሌላ ማንኛውም የምርቱ አካል የሆነ መሰል ነገር ማለት ነው፤

2.4. "ባዕድ ነገር" ማለት ለውጪ ገበያ ከሚዘጋጁ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች ውስጥ በምርት ዝግጅት ወቅት የሚወጣ ድንጋይ፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ አፈር ወይም ሌላ ማንኛውም የምርቱ አካል ያልሆነ መሰል ነገር ማለት ነው፤

2.5. "ላኪ" ማለት እንደ አግባቡ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹትን የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ማለት ነው፤

2.6. "አዘጋጅ" ማለት እንደ አግባቡ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶችን የማዘጋጀት አገልግሎት የሚሰጥ ማለት ነው፤

2.7. "አግባብ ያለው አካል" ማለት የንግድ ሚኒስቴር ወይም በክልል መንግስታት/በከተማ አስተዳደሮች ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ማለት ነው።

2.8. "አግባብ ያለው ሴክተር መ/ቤት" ማለት ለውጪ ገበያ ከሚዘጋጁ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የሚወጣውና ለሰው ፍጆታ የሚውለው ብጣሪ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ላላቸው ድርጅቶች ለሰው ቀለብ እንዲውል በደረሰኝ መሸጡን ወይም ለእንስሳት ፍጆታ የሚውለው ብጣሪ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ላላቸው ድርጅቶች ለእንስሳት መኖ እንዲውል በደረሰኝ መሸጡን ወይም መወገድ ያለበት ብጣሪ በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ በታወቀ ቦታ ላይ በጥንቃቄ መወገዱን የሚከታተል መ/ቤት ማለት ነው።

3. የተፈፃሚነት ወሰን

3.1. ይህ መመሪያ በቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች ላኪዎች፣ አዘጋጆች እና አቀናባሪዎች እንዲሁም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከምርቶቹ ዝግጅት ጋር ግንኙነት ባላቸው አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ

3.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከህዳር ወር 2003 ዓ/ም ጀምሮ በላኪዎች መጋዝን ተከማችቶ በሚገኘው ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ብጣሪ እና ባዕድ ነገር ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. ለውጪ ገበያ ከሚቀርቡ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች በኩንታል የሚወጣ አማካይ የብጣሪ መጠን በመቶኛ

| ተ.ቁ | የምርት አይነት | ባዕድ ነገር (ድንጋይ፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ አፈር፣ አቧራ) | የተጎዳ ፍሬ (የተሰባበረ፣ የተጨማደደ፣ ቀለሙን የቀየረ/የገረጣ፣የሻገተ፣የ ነቀዘ፣ የቀጨጨ ፍሬ) | ገለባና የአረም ዘር | ጠቅላላ የብጣሪ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቅባት እህሎች | | | | |
| 1.1 | ነጭ የሁመራ ሰሊጥ | 3.25 | 2.25 | 0.5 | 6 |
| 1.2 | ነጭ የወለጋ ሰሊጥ | 3.5 | 2.5 | 0.5 | 6.5 |
| 1.3 | ኑግ | 6.5 | 3 | 1 | 10.5 |
| 1.4 | ተልባ | 3.5 | 2 | 0.5 | 6 |
| 1.5 | ጎ/ዘር | 4.5 | 2 | 1.5 | 7 |
| 1.6 | ለውዝ (የተፈለፈለ) | 2.5 | 3.5 | 0.5 | 6.5 |
| 1.7 | የጎሎ ፍሬ (የተፈለፈለ) | 2 | 1.5 | - | 3.5 |
| 1.8 | ሱፍ | 1.5 | 1 | 0.5 | 3 |
| 1.9 | የዱባ ፍሬ | 4 | 7.5 | 0.5 | 12 |
| 2 | የጥራጥሬ ምርቶች | | | | |
| 2.1 | ነጭ ቦለቄ | 5.5 | 7 | 1 | 13.5 |
| 2.2 | ቀይ ቦለቄ | 6.5 | 6.5 | 1 | 14 |
| 2.3 | ዥንጉርጉር ቦለቄ | 5.5 | 7 | 1 | 13.5 |
| 2.4 | ፒንቶ ፒን | 5.5 | 7 | 1 | 13.5 |
| 2.5 | የእርግብ አተር | 6 | 4.5 | 0.5 | 11 |
| 2.6 | ቡላ ጠፍጣፋ ቦለቄ | 5 | 6 | 1 | 12 |
| 2.7 | ዱቤ ሽምብራ | 5.25 | 4.75 | 0.75 | 10.75 |
| 2.8 | ካቡሊ ሽምብራ | 4.25 | 3.5 | 0.75 | 8.5 |
| 2.9 | አኩሪ አተር | 5.75 | 5 | 0.75 | 11.5 |
| 2.10 | ግብጦ | 4.5 | 5.3 | 1 | 9.5 |
| 2.11 | ባቄላ | 5.5 | 4.75 | 0.75 | 11 |
| 2.12 | ማሾ | 4.5 | 8 | 0.75 | 13.25 |
| 2.13 | ጓያ | 6.5 | 5 | 0.5 | 12 |
| 2.14 | ምስር | 5.5 | 5 | 0.5 | 11 |

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

5. አንቀጽ 4 ላይ በተቀመጠው የብጣሪ መጠን መሠረት ለውጪ ገበያ ከሚቀርቡት የቅባት እህሎችና የጥራጥሬ ምርቶች የሚወጣው ብጣሪ ግልጋሎት ላይ የሚውልበት ወይም የሚወገድበት ሁኔታ

5.1. በምርት ዝግጅት ወቅት የሚወጣውን ድንጋይ፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ አፈር እና አቧራ የሕብረተሰቡን ጤና በማይጎዳና የአካባቢ ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ በጥንቃቄ በማስወገድ የተወገደበትን ቦታ እና የተወገደውን መጠን ጠቅሶ አግባብ ላለው አካል እና ለሚመለከተው አግባብ ያለው ሴክተር መ/ቤት በወቅቱ ማሳወቅ አለበት።

5.2. በብጣሪ መልክ የሚወጣው የተሰባበረ፣ የተጨማደደ፣ ቀለሙን የቀየረ/የገረጣ፣ የሻገተ፣ የነቀዘ እና የቀጨጨ ፍሬ እንዲሁም የምርት ገለባ እና የአረም ዘር ለእንስሳት መኖ ወይም ለሰው ግልጋሎት መዋል የሚችል ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ ፍቃድ ላላቸው ድርጅቶች በደረሰኝ በመሸጥ አግባብ ያለው አካል ወይም የሚመለከተው አግባብ ያለው ሴክተር መ/ቤት ሲጠይቅ ደረሰኙን ማሳየት አለበት።

5.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ለይ የተገለፀው ብጣሪ ለሰው ግልጋሎት ወይም ለእንስሳት መኖ የማይውል ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተደነገገው መሠረት ማስወገድ አለበት።

6. የላኪዎች ወይም የአዘጋጆች ግዴታ

6.1. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎችና የጥራጥሬ ምርቶችን ብጣሪ ከዋናው ምርት በጥራት በመለየት ለሰው ግልጋሎትና ለእንስሳት መኖ የሚውለውን እና ጥቅም የማይሰጠውን ባዕድ ነገር በዓይነት በመለየት ለየራሱ በተዘጋጀ ቦታ ላይ በአግባቡ ለየብቻው የማከማቸት፤

6.2. ይህንን መመሪያ እና በዚህ መመሪያ ላይ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ለማስፈፀም አግባብ ያለው አካል የሚያወጣቸውን አሰራሮች የማክበር፤

6.3. ከዚህ መመሪያ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ህጎችና አሰራሮች የማክበር፤

6.4. በምርት ቆጠራ ወቅት ወይም በማንኛውም ጊዜ አግባብ ያለው አካል ወይም የሚመለከታቸው አግባብ ያላቸው ሴክተር መ/ቤቶች መረጃ በሚጠይቁ ጊዜ አስፈላጊውን መረጃ በተሟላ ሁኔታ የመስጠት እንዲሁም ለሰው ግልጋሎት እና

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት
ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት